የሰ/መ/ቁጥር---241752

ቀን- ሰኔ 26 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች:- ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሎሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች:- አቶ መላኩ ካሳዉ ዓለሙ አልቀረቡም

ተጠሪ:- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ነ/ፈጅ ዮዲት ደረጀ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የሥራ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93232 ታሕሳስ 06 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 294208 ጥር 05 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

አመልካች ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ ይዘት:- አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት ዉስጥ ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ የሥራ መደብ ላይ ሲሠሩ ቆይተዉ ነሐሴ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጡረታ በመዉጣታቸዉ የስራ ዉላቸዉ መቋረጡንና በወቅቱም ደመወዛቸዉ ብር 15,774 የነበረ መሆኑን፤ የ2013 እና 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሲከፍዉ ከ2003 እስከ 2012 ዓ.ም ያለዉ የ462 ቀናት የዓመት እረፍት ግን አለመክፈሉን፤ ተጠሪ የአመልካችን የዓመት እረፍት እያስተላለፈ የተጠራቀመ በመሆኑ ያልተጠቀሙበት እርፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸዉ፤ እንዲሁም በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ሙሉ ዓመት ያገለገሉ ሲሆን ለሠራተኞች የ አንድ ወር ተኩል የማትጊያ/ቦነስ ክፍያ የከፈለ ቢሆንም ለአመልካች የስራ ዉል የተቋረጠ ስለሆነ የቦነስ ክፍያ አይመለከትህም በሚል ያልከፈላቸዉ በመሆኑና ዓመቱን ሙሉ የሠራና ለትርፉ አስተዋጽኦ ያደረገበት በመሆኑ የቦነስ ክፍያ እንዲከፈለዉ እንዲሁም ክፍያዎችን ላዘገየበት ካሳ የ3 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸዉ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ የዓመት እረፍት ጥያቄዉ በይርጋ የታገደ ነዉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲያቀርብ በፍሬ ጉዳይ መልሱ ደግሞ አመልካች የስራ ዉላቸዉ በጡረታ ምክንያት ነሐሴ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

01 ቀን 2014 ዓ.ም ተቋርጧል፡፡ በወቅቱም የ2013 ዓ.ም 51 ቀናት፤ የ2014 ዓ.ም 53 ቀናት እንዲሁም የ2015 ዓ.ም 5 ቀናት በድምሩ የ109 ቀናት እረፍታቸዉ በገንዘብ ተቀይሮ ተከፍሏቸዋል፡፡ አመልካች በጥቅሉ ያልተጠቀሙበት 462 የስራ ቀናት አልተጠቀምኩም በማለት መጠየቃቸዉ የትኛዉ ዓ.ም ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ አያስቀምጥም፤ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 79(4) የዓመት እረፍት ከ2 ዓመት በላይ እንዳይተላለፍ በግልጽ ደንግጓል፡፡ አመልካች እረፍታቸዉን መጠቀም የነበረባቸዉ አጣዳፊ ሥራዉን እንደጨረሱ ወይም እረፍታቸዉ እስከተላለፈበት ሁለት ዓመት ድረስ ነዉ እንጂ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2012 ዓ.ም ያለዉ ከ2 ዓመት በላይ ሊተላለፍ ስለማይችል ሊጠይቁ አይችሉም፡፡ በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 163(3) መሠረት በ6 ወር ጊዜ ዉስጥ ያልጠየቁት በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፡፡

የቦነስ ክፍያን በተመለከተ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 64758 ቦነስ ሊከፈል የሚገባዉ በአሠሪና ሠራተኛ ስምምነት መሠረት ነዉ በሚለዉ ገዥ ትርጉም መሠረት በተጠሪ ድርጅት እና በሠራተኛ ማህበሩ ለ2ኛ ጊዜ ድርድር ተደርጎ መጋቢት 2011 ዓ.ም በጸደቀዉ የሕብረት ስምምነት መመሪያ አንቀጽ 16.8 መሰረት ቦነስ የሚከፈለዉ በድርጅቱ የፋይናንስና የሥራ አፈጻጸም እንዲሁም በሠራተኛዉ የስራ አፈጻጸም ዉጤት ላይ ተመስርቶ የድርጅቱን ትርፋማነትና አቋሙን ባገናዘበ መልኩ በሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ሲወሰንና ሲጸድቅ በድርጅቱ በሚወጣ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተግባራዊ በማድረግ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት ጳጉሜ 2 ቀን 2014 ዓ.ም የወጣዉ የቦነስ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ የቦነስ ክፍያ የሚፈጸመዉ በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ሥራ ላይ ለነበሩና አሁንም የሥራ ዉላቸዉ ላልተቋረጠ ሠራተኞች በመሆኑና መመሪያዉ ሲወጣ የአመልካች የሥራ ዉል ተቋርጦ ስለነበረ ክፍያዉ አይገባቸዉም፡፡ የአመልካች የስራ ዉል በጡረታ ምክንያት ሲቋረጥ ተጠሪ ዘንድ ያላቸዉ ሕጋዊና የታመኑ ክፍያዎች በሙሉ የተከፈላቸዉና የዘገየ ክፍያ ባለመኖሩ ከክፍያ መዘግየት ጋር በተያየዘ ያቀረቡት የ3 ወር የካሳ ክፍያ የሕግ መሠረት የለዉም በማለት ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ የቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ክርክር መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 79 መሠረት የዓመት እርፍት ከሚቀጥለዉ 2 ዓመት በላይ ሊራዘም የማይችል በመሆኑና የአመልካች የሥራ ዉል በጡረታ የተቋረጠዉ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች መጠየቅ የሚችሉት በእያንዳንዱ ዓመት ባለዉ 2 ዓመት ጊዜ ዉስጥ እንጂ የስራ ዉላቸዉ እስኪቋረጥ ጠብቀዉ ስላልሆነ የመጠየቅ መብታዉ በይርጋ ታግዷል በማለት ሕዳር 08 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የዓመት እፍትን አስመልክቶ የቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

በመቀጠል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቦነስ ክፍያ በተመለከተዉ የዳኝነት ጥያቄ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶና መርምሮ የተጠሪ ድርጅት ጳጉሜ 2 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ በከፍተኛ አመራር ቦርድ ዉሳኔ መሰረት የማትጊያ ክፍያ አፈጻጸም በ2014 ዓ.ም ሥራ ላይ ለነበሩ እና አሁንም የስራ ዉላቸዉ ላልተቋረጠባቸዉ ሠራተኞች መሆኑን የወሰነና መመሪያዉ በወጣበት ወቅት አመልካች በጡረታ የስራ ዉላቸዉ የተቋረጠ በመሆኑ ለአመልካች የቦነስ ጥያቄ የሚከፈልበት አግባብ የለም በማለት የአመልካችን

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

የቦነስ ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ አመልካች ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት፡- አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸዉ ለመጠየቅ የሚችሉት የሥራ ዉሉ ሲቋረጥ መሆኑን፣ የሥራ ዉላቸዉ ተቋርጦ 6 ወር ሳይሞላቸዉ ክስ መስርተዉ እያለ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ ስህተት ነዉ፡፡ አዋጁ የዓመት እረፍት ከሁለት ዓመት በላይ አይተላላፍም ይላል እንጂ ተላልፎ ቢገኝ ምን ይሆናል ለሚለዉ ጥያቄ መልስ አይሰጥም፡፡ የዓመት እርፍቱ ሲተላለፍ የኖረዉ በተጠሪ ምክንያት ነዉ፡፡ ስለሆነም ይርጋዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 ድንጋጌ አንጻር ታይቶ የ462 ቀናት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል ሊወሰን ይገባል፡፡ የቦነስ ክፍያን በተመለከተ አመልካች በበጀት ዓመቱ ለአሠሪዉ ትርፋማነት አስተዋጽኦ አድርጎ አሠሪዉ ቦነስ ለሠራተኞቹ የሚከፈል ከሆነ በበጀት ዓመቱ ሥራ የለቀቀ ሠራተኛም ቢሆን ቦነስ ሊከፈለዉ እንደሚገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20869 ገዥ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ በዚሁ አግባብ ተመልክቶ ሊወሰን እየተገባዉ ተጠሪን በማመን በሚመስል መልኩ የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ቦነስ ክፍያ እንዲከፈል እንዲወሰን እንዲሁም የስራ ዉል በተቋጩ በ7 ቀናት ዉስጥ ክፍያዎቹ ባለመከፈላቸዉ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ እንዲከፈል እንዲወሰንላቸዉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የቦነስ ክፍያ አይከፈለዉም የተባለበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለአቤቱታዉ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 64758 በሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ቦነስ ሊከፈል የሚገባዉ በአሠሪና ሠራተኛ ስምምነት መሠረት እንጂ አስገዳጅ እንዳልሆነ በገለጸዉ መሠረት መጋቢት 2011 ዓ.ም በጸደቀዉ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 16.8 እና 16.8.2 መሠረት ተጠሪ ድርጅት ጳጉሜ 2 ቀን 2014 ዓ.ም የወጣዉ የቦነስ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ የቦነስ ክፍያ የሚፈጸመዉ በ2014 በጀት ዓመት ሥራ ላይ ለነበሩ እና አሁንም የሥራ ዉላቸዉ ላልተቋረጠ ሠራተኞች መሆን እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑና የአመልካች የስራ ዉል ይህ መመሪያ ከመዉጣቱ በፊት የተቋረጠ በመሆኑ አመልካች በበጀት ዓመቱ ስላገለገሉ ብቻ እንደመብት የቦነስ ክፍያ ተጠሪ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተገቢነት የለዉም፡፡ ተጠሪ ምንም ዓይነት የታመነበትን ክፍያ ያላዘገየ በመሆኑ የ3 ወር ደመወዝ በቅጣት መልክ የሚከፍልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 03 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ አመልካች ሥራ ላይ በነበረበት የ2014 በጀት ዓመት ቦነስ ክፍያ ሲፈጸም ጡረታ በመዉጣቱ የስራ ዉሉ ተቋርጧል በሚል የቦነስ ክፍያ አይከፈለዉም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉ የስራ ዉል ነሐሴ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጡረታ በመዉጣታቸዉ ተቋርጧል፡፡ ተጠሪ የ2014 በጀት ዓመት የቦነስ/የማትጊያ ክፍያ የፈጸመዉ የተጠሪ ድርጅት ከፍተኛ አመራር ቦርድ በቃለ ጉባኤ ወስኖ ጳጉሜ 02 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተሰጠ መመሪያ ነዉ፡፡ መመሪያዉ ቦነስ ለሠራተኛዉ የሚከፈለዉ በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ሥራ ላይ የነበረ እና የቦነስ ክፍያ ሲፈጸም የሥራ ዉሉ ያልተቋረጠ ወይም ሥራ ላይ ላሉ ሠራተኞች መሆኑ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ለአመልካች የቦነስ ክፍያ ለመክፈል አይገደድም በማለት ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ ቦነስ አሠሪዉ ተገድዶ የሚፈጽመዉ ክፍያ ሳይሆን አሠሪዉ በሚያወጣዉ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚፈጸም በመሆኑና በወጣዉ መመሪያ መሠረት አመልካች ክፍያዉ እንዲፈጸምላቸዉ የሚደግፋቸዉ አይደለም በማለት ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም አጥብቀዉ የሚከራከሩት ቦነስ የሚከፈለዉ ሠረታኛን ለወደፊቱ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ ሠራተኛዉ ለአሠሪዉ ትርፋማነት ላደረገዉ አስተዋጽኦ ጭምር መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 20869 ከሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ታይቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ነዉ፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 53(2ሐ) ጉርሻ(ቦነስ) የሠራተኛዉ ደመወዝ ሳይሆን ከአሠሪዉ ለሠራተኛዉ በጉርሻ መልክ የሚከፈል ክፍያ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በርግጥ ቦነስ ክፍያ ለሠራተኛ የሚከፈለዉ በሥራ ላይ ያለ ሠራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሠራ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራዉ ሥራ ለአሠሪዉ ትርፋማ ዉጤት በማስገኘቱ የትርፍ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል በመሆኑ ሠራተኛዉ ሥራዉን ቢለቅም ቦነሱ ሊከፈለዉ እንደሚገባ ሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ 20869 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 101825 ስለቦነስ አከፋፈል የተመለከተ የሕብረት ስምምነት በሌለበት ሠራተኛዉ ሥራዉን ቢለቅም አስተዋጽኦ ባደረገዉ የትርፋማነት ዉጤት ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚገባ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል ሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ 202839 በሰጠዉ ዉሳኔ በህብረት ስምምነት በሌላ አኳኃን ካልተመለከተ በስተቀር የቦነስ ክፍያ በአሠሪዉ መልካም ፈቃድ የሚፈጸም እንጂ በአሠሪዉ ላይ በሕግ የተጣለ ግዴታ ባለመሆኑ የክፍያዉን አፈጻጸም እንዲሁም የሚያስከትለዉን ሕጋዊ ዉጤት አስመልክቶ አሠሪዉ በሚያወጣዉ ደንብ(መመሪያ) ወይም የቃለ-ጉባኤ ዉሳኔ መሠረት ተግባራዊ ሊያደርገዉ የሚችለዉ እንጂ እንደ ሌሎች የሠራተኞች መሠረታዊ መብቶች በአዋጁ ከተመለከተዉ ዝቅተኛ የሥራ ሁኔታዎች መስፈርት አንጻር ታይቶ ዉጤት እንዲኖረዉ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰዉ የአዋጁ ድንጋጌና ገዥ ትርጉሞች መገንዘብ

Daniel Fikadu Law Office

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

የሚቻለዉ የጉርሻ(ቦነስ) አከፋፈል በተመለከተ በሕብረት ስምምነት ወይም በአሠሪዉ በወጣ መመሪያ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ በማይኖርበት ወቅት ሠራተኛዉ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የሥራ ዉሉ ቢቋረጥም አስተዋጽኦ ባደረገዉ የትርፋማነት ዉጤት ተጠቃሚ ሊሆን ስለሚገባዉ ጉርሻ(ቦነስ) ሊከፈለዉ የሚገባዉ ሲሆን፤ በሕህብረት ስምምነት ወይም በአሠሪዉ በወጣ መመሪያ ክፍያ ከመከፈሉ አስቀድሞ የስራ ዉሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ ቦነስ እንደማይከፈል የተቀመጠ ግልጽ ቅድመ ሁኔታ ሲኖር ደግሞ ከክፍያዉ በፊት የስራ ዉሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ ቦነስ ለመክፈል አሠሪዉ የማይገደድ መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በተጠሪና በመሠረታዊ የሠራተኛ ማሕበር መካከል ለሁለተኛ ጊዜ መጋቢት 2011 ዓ.ም የተደረገዉ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 16.8.2 ስር ስለቦነስ አከፋፈል በተመለከተ በየሥራ ሂደቱ(ዘርፉ) የስራ አፈጻጸም ዉጤት ላይ ተመስርቶ የድርጅቱን ትርፋማነትና አቅሙን ባገናዘበ መልክ ተጠሪ ሊሰጥ ይችላል በማለት ተመልክቷል፡፡ ይህ የሕብረት ስምምነት ድንጋጌ ቦነስን አስመልክቶ ተጠሪ ላይ በአስገዳጅነት ለሠራተኛዉ ቦነስ የሚከፍልበትን ሁኔታ የሚያስቀምጥ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሥራ ዘርፉን አፈጻጸም፣ የድርጅቱን ትርፋማነትና የመክፈል አቅሙን አገናዝቦ ተጠሪ ሊከፍል እንደሚችል ከማስቀመጥ ባለፈ የትኛዉ ሠራተኛ የቦነስ ክፍያዉ ተጠቃሚ እንደሚሆን እና የትኛዉ ተጠቃሚ እንደማይሆን በግልጽ ተጠሪን በሚያስገድድ ሁኔታ የተቀመጠ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በቦርድ አስወስኖና መመሪያ አዉጥቶ የቦነስ ክፍያን እንዳይፈጽም የሚከለክለዉ ነገር የለም፡፡

ምንም እንኳ የበጀት ዓመቱ ካለፈ በኋላ ቢሆንም ክፍያዉ ከመፈጸሙ በፊት የቦነስ ክፍያዉ የሚገባቸዉን ሠራተኞች መለየት የሚያስችል መስፈርት ያካተተ የክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ጳጉሜ 02 ቀን 2014 ዓ.ም ተጠሪ አዉጥቷል፡፡ በመመሪያዉ መሠረት አንድ ሠራተኛ የቦነስ ተከፋይ ለመሆን በ2014 በጀት ዓመት ሥራ ላይ ሆኖ ለአፈጻጸሙ አስተዋጽኦ ከማድረግ በተጨማሪ ክፍያዉ ሲፈጸም ሥራ ላይ ያለ ወይም የሥራ ዉሉ ያልተቋረጠ ሠራተኛ መሆን እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ምንም አንኳ በ2014 በጀት ዓመት ሥራ ላይ የነበሩና ለአፈጻጸሙ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም በመመሪያዉ መሠረት ክፍያ በሚፈጸምበት ወቅት ጡረታ በመዉጣታቸዉ የስራ ዉላቸዉ የተቋረጠ በመሆኑ የቦነስ ክፍያ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አግባብ የለም፡፡ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 20869 አስቀድሞ የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ መዝገብ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ጉዳይ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት ያለዉ ባለመሆኑ አመልካች አስቀድሞ በተጠቀሰዉ መዝገብ የተሰጠዉን ገዥ ትርጉም መሠረት በማድረግ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተጠሪ ድርጅት ከፍተኛ የአመራር ቦርድ ባወጣዉ መመረያ የተቀመጠዉን ቅድመ ሁኔታ አላሟላም በሚል ተጠሪ ለአመልካች ቦነስ ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ከ2003 እስከ 2012 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ሳይጠቀሙ የቀሩትን የ 462 ቀናት የዓመት እረፍት አስመልክቶ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸዉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በስር ፍ/ቤት ዉድቅ መደረጉን አስመልክተዉ በሰበር አቤቱታቸዉ ያቀረቧቸዉን ቅሬታዎች የዓመት እርፍት ፈቃድ ከሚቀጥለዉ ሁለት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

Daniel Fikadu Law Office

ዓመት ጊዜ በላይ አይራዘምም የሚለዉን በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 79(4) ድንጋጌን ክልከላ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልንም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የቦነስ ክፍያ ለአመልካች ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ ከሁለት ዓመት በላይ ተላልፏል የተባለዉን የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93232 ታሕሳስ 06 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 294208 ጥር 05 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ብይን የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ገ

Daniel Fikadu Law Office

Daniel Fikadu Law Office

Daniel Fikadu Law Office

Daniel Fikadu Law Office

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT